# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ቁጥር ፩፤ሰኔ ፳፻፲፪ ዓ.ም

**ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ** በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት፡፡



“ለልጆቻችን መልካም ተግባራትን በማስተማር የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ እንችላለን፤ ከዚህ ትልም መዳረሻ መንገዶች አንዱ ደግሞ ህፃናት ጥብቅ ቁርኝት ከተፈጥሮ ጋር እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡”

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ

## በዚህ እትም. . .


| | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ስልት ትግበራ ዳሰሳ | 2 |
| ዜናዎች | 2 |
| የኢትዮጵያ የሀይል ተደራሽነት ጥረትና የማሳኪያ መዋለ ንዋይ አሰባሰብ ትልም | 4 |
| ሁነቶች | 4 |
| ልዩ ልዩ ህትመቶች | 5 |





**ዋና አዘጋጅ፥** ንጉሱ ለማ ገብሬ

**አዘጋጆች፥** ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ እና ሮቢ ረዳ

**አምደኞች፥** ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ፣ መንሱር ደሴ እና መህመድ አንዶሼ

**ግራፊክስና ሌይአውት፥** አርሴማ አንዳርጋቸው

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ
ቅፅ ፩፣ቁጥር ፩

# ዜናዎች

## አረንጓዴ አሻራ

የዓለም አካባቢ ቀን በተከበረበት ግንቦት 28፣ 2012 ዓ.ም የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር ዐብይ አህመድ የበጀት ዓመቱን የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር አስጀመሩ፡፡

መርሀ ግብሩ ባለፈው ዓመት ተጀምሮ 4ቢሊዮን ችግኞች የተተከሉበትንና "አረንጓዴ አሻራ" የሚል ስያሜ የተሰጠውን ሀገራዊ የችግኝ ተከላ በማስቀጠል 5ቢሊዮን ያህል የዛፍ ችግኞችን ለመትከል ያለመ ነው፡፡

የበጀት ዓመቱ የአረንጓዴ ልማትና ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር የኮቪድ-19 ወረርሽኝ አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን በመገንዘብ በሀገር ደረጃ ዘመቻው የዜጎችን የኮሮና ቫይረስ ተጋላጭነት በሚያስቀር መልኩና በጤና ተቋማት የተቀመጡ ደረጃዎችን በጠበቀ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡

ይህንን ርዕሰ ጉዳይ የተመለከቱ መረጃዎችን በቀጣይ ህትመታችን እናቀርብላችኋለን ፡፡ ምንጭ

## የዳሰሳ ጥናት፤ በዘመነ ኮሮና የኢንተርኔት ተሳትፎ ሚና

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በመላ ዓለም በተጋረጠበትና ዓለማቀፍ ጉዞ በተዘጋበት በዚህ ወቅት ሰዎች እንዴት ፊት ለፊት መገናኘት እንደሚኖርባቸው መላ መተዋል፡፡ በዚህ ረገድ ተመራጭ የሆነው ዘዴ በበየነ መረብ ላይ በሚተገበሩ መተግበሪያዎች መጠቀም መተኪያ የሌለው መፍትሄ ሆኗል፡፡ በዓለማችን የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ይህ ዘዴ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉበት ነው፤ የዓለማችን የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ህዝቦች ከዚህ አኳያ ያሉበትን ሁኔታ ለማገናዘብ ይረዳዋ ዘንድ የርሶን የበየነ መረብ ተሞክሮና ያጋጠሙዎትን ተግዳሮቶች በአጭሩ ለመረዳትና ችግሩን ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ ከታች ያለውን ማስፈንጠሪያ በመጫን ጥናቱን ያግዙ፡፡ ምንጭ

## የኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆነ የልማት ጉዞ፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ትግበራ የዳሰሳ ጥናት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ

- በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የተዘጋጀ

ከ2003 ዓ.ም አንስቶ ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆነ የልማት አቅጣጫ ኢትዮጵያ ቅድሚያ ከምትሰጣቸው አማራጮች አንዱ ሁኖ ቆይቷል፡፡ ከ2003-2011 ዓ.ም የነበረውን የትግበራ ደረጃ ለመዳሰስና የወደፊት አቅጣጫዎችን ለማመላከት ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራ የዳሰሳ ጥናት በዓለም ባንክ ድጋፍ እያገባደድንው ባለው ዓመት ተከናውኗል፡፡ ይህ ፅሁፍም የዳሰሳ ጥናት ሪፖርቱ ላይ የተገለፁትን ቁልፍ ግኝቶችና ምክረ ሀሳቦች ጠቅለል ባለ ሁኔታ ያቀርባል፡፡

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት፤ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት የተለመደውን አሰራር ብንከተል በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ጋር ሲነፃፀር በ64 በመቶ (255 ሚ.ሜ.ቶ የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ) የመቀነስ ኢላማ አስቀምጧል፡፡ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ በሚል ራዕይ፤ እንዴት መዋቅራዊ የኢኮኖሚ የአሰራር ለውጥና ውጤታማነትን በማሳደግ፤ ሀገራችን ፈጣን ኢኮኖሚን በመከተል ወደከባቢ አየር ልትለቅ ትችል የነበረውን ተጨማሪ የሙቀት አማቂ ጋዞችን እንዴት ማሰቀረት እንደሚቻል ያስቀምጣል፡፡




**ምስል፤** የኢትዮጵያ የዝቅተኛ ካርቦን ልቀት ገፅታ የሚያሳይ ግራፍ; (ምንጭ፤ ለተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንቬንሽን እአአ በ2015 ኢትዮጵያ ካስገባችው የካርበን ልቀት ቅነሳ ዕቅድ የተወሰደ፡፡)

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ከአለም ጋር ሲነፃፀር የሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመልቀቅ ያላት ድርሻ 0.04% ብቻ ሁኖ እያለና በዚህም 93ኛ ላይ የተቀመጠች ቢሆንም አረንጓዴ ኢኮኖሚ መንገድ በመከተል ለሙቀት አማቂ ጋዞች ቅነሳ የላቀ የልማት ፍኖተ ካርታ ተከትላለች፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገበች ያለች ሀገር ብትሆንም በአመት 790 የአሜሪካ ዶላር ገቢ ብቻ በማግኘት በአለም ድሀ ከሚባሉት ሀገራት ተርታ ተሰልፋ ትገኛለች።

**ከገፅ 2 የቀጠለ...**

በተጨማሪም 110 ሚሊዮን ህዝብ በመያዝ ከአፍሪካ በህዝብ ብዛት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት። በዚህም ምክያት ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ካሉት ሀገራት፤ በረዥም ጊዜና በልማት ዘርፍ ላይ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ተፅዕኖ ለመመከትና በተቀናጀ መልኩ ምላሽ ለመስጠት ቁርጠኛ አቋም ከያዙት ሀገራት መካከል የምትጠቀስ አድርጓታል፡፡

የዳሰሳ ጥናት ሪፖርቱ ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራ ዙሪያ ቅድሚያ ለምትሰጣቸው ጉዳዮች እንደ ማስተሰረያ፣ ማጣጣሚያ፣ ፋይናንስ፣ ተቋማዊና የፖሊሲ ልማት ተግባራት ዙሪያ ሲከናወኑ የነበሩ ጥረቶችን በጥልቀት መርምሮ የተገኙ ስኬቶችና መሰናክሎችን አስቀምጧል፡፡

ስኬቶችን በተመለከተ በርካታ ውጤታማ የነበሩ ተግባራት እየተከናወኑ የቆዩ ሲሆን፤ ይህም መንገድ በተጨባጭ የ1ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሼን ዕቅድ ኢላማዎችን ለማሳካት አስተዋፅዖ ያደረገ ሲሆን፤ በተጨማሪም የሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመቀነስና ይህን ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል፡፡

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት ልዩ የሚያደርገው፤ አጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ማተኮሩና ዘርፎችን ምሉዕ በሆነ ሁኔታ ማካተት መቻሉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስልቱ በሀገሪቱ ሁሉን አቀፍ በሆነው የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካቷል፡፡ በሀገሪቱ ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገባ ፍላጎቶች መሰረት፤ የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚከናወኑ የማጣጣሚያ ተግባራት በአብዛኛው በግብርናው ዘርፍ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

በዚህ ረገድ የአየር ንብረት ለውጥ የመቋቋም አቅም የሚፈጥሩና በዝቅተኛ የግብርና መስክ ለተሰማሩና የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ለአየር ንብረት አልበገሬነትን የሚገነቡ በርካታ በይዘታቸው ሰፊ የሆኑ የምግብ ዋስትናና ለግብርና ምርታማነት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ፕሮግራሞች ከ2003-2011 ዓ.ም ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡

እንደ ምሳሌነትም አንዳንድ ስልታዊ የልማት ፕሮግራሞች፤ የምርታማነት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም፣ የግብርና እድገት ፕሮግራም፣ የዘላቂ መሬት አጠቃቀም ፕሮጀክት እና አሳታፊ አነስተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን ጨምሮ መጥቀስ ይቻላል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በደኑ ዘርፍ በርካታ ከማስተሰረያና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ስቦ ማስቀረት ከሆነው ዋነኛ የተቋቋሙበት አላማቸው ባለፈ፤ የአየር ንብረት ለመቋቋምም አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ የማስተሰረያ ትግበራን በተመለከተ REDD+ ፕሮግራምና ግዙፍ የሆኑት ኢነርጂና ትራንስፖርት ላይ ያተኮሩት ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ኢትየጵያ በአየር ንብርት ልውጥ ፋሲሊቲ ሴክሬታሪያት በኩል ለአየር ንብረት ተግባራትን ለማከናወን የሚረዳ በርካታ ሀብት ማፈላለግ ችላለች፡፡

**የዳሰሳ ጥናቱ ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩትን አስፈላጊ የሆኑ ምክረ ሀሳቦችን አስቀምጧል፤**

- የተለያዩ ስርዓቶችን ማስቀጠልና ወደ ትግበራ ማስገባት አስፈላጊ ሲሆን በዋንኛነትም አሁን ያለውን የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ (MRV) ማዕቀፍ በሁሉም ደረጃ መከለስና አመታዊ ሪፖርት ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ በግልፅ አመላክቷል፡፡
- ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ ኢላማዎችዋን እያስቀመጠችና ትግበራውን እያጠናከረች በሀገራዊ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ፤ ለአየር ንብረት ተጋላጭነት ዙሪያ መነሻ መረጃ ለማግኘትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ለማስቀመጥ እንዲረዳ ጥልቅ የሆነና ዘርፎች ላይ ያተኮረ የአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎችና ተጋላጭነትን ማጥናት ይጠበቅባታል፡፡
- ተደራሽና ዝርዝር የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ መረጃዎች መከታተልና የማስተሰረያ ትግበራ ደረጃን ለማወቅ የሚያስችል የተጠናከረ የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ የመረጃ ቋት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት በሁሉም ደረጃ መጠቀም የሚያስችሉ የአየር ንብረት ለውጥ አመላካቾችን መለየትና ለተግባሪና አስተባባሪ አካላት ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡ ዘርፎችም የሚያዘጋጁት ለአይር ንብረትለውጥ የማይበገር አረንገዴ ኢኮኖሚ የተካተተበት ዕቅድና ሪፖርትበተለዩት አመላካቾች መሰረት መሆን ይጠበቅበታል፡፡
- የገንዘብ ሚኒስቴር በሁሉም የመንግስት ተቋማት ስር ለአየር ንብረት ትግበራ ከመንግስት የተመደበውን በጀት ለይቶ ለማወቅ እንዲረዳ የህዝብ ወጪ መከለሻ ማዕቀፍ መዘርጋት ይጠበቅበታል፡፡ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ፋሲሊቲ በአየር ንብረት ፋይናንስ በጀት መረጃ ዙሪያ በብሄራዊና ዘርፍ ደረጃ ዓመታዊ ዘገባ ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡
- ምንም እንኳን በ2008 ዓ.ም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ፋሲሊቲ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያሳድግ ስልት አዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም ሰነዱ ምን በማከናወንና እንዴት የሚሉት ስልታዊ መመሪያዎች ባለማመላከቱ ውጤታማ መሳሪያ መሆን አልቻለም፡፡ ፋሲሊቲውና ዘርፎች አዲስ እየተፈጠሩ ያሉ የግል ዘርፎች በመኖራቸው፤ ከግል ድርጅቶች ጋር የውይይት መድረክ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የእውቀትና መረጃ ለማስተዳደር እንዲያስችል አየር ንብረት ለውጥ የሚመለከቱ መረጃዎችን መያዝና ማስቀመጥ የሚያስችል ማእከላዊ መረጃና የእውቀትና መረጃ ስርዓት አስተዳደር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ዘርፎችም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስርዓት በሁሉም ደረጃ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዘርፎች የሚዘረጋው ስርአት ማዕከላዊ ከሆነው ስርዓት ጋር የተቀናጀ መሆን ይጠበቅበታል፡፡
- የዳሰሳ ጥናቱ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት የሚኖረውን ከፍተኛ አስተዋፅዖና የተለየ የአየር ንብረት ለውጥ ሰነድ ስለመሆኑ እውቅና ይሰጣል፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ በትግበራው ላይ ያላትን ሚና እያስቀጠለችና ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግቧን ማሳካቷን እየቀጠለች፤ ትግበራውን ለመለካት የሚያስችል ስርዓት የማጠናከር ስራዎች ላይም ትኩረት እንድትሰጥ ምክረ ሀሳብ ተቀምጧል፡፡

## ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች ተሠርዘዋል ወይም ተራዝመዋል። ይሁንና በዚሁ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ቀጣዮቹ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ተካሂደዋል፤ አብዛኞቹ ሁነቶችም ለተሳታፊዎች ተደራሽ ተደርገዋል። እያንዳንዱን ሁነቶችን አስመልክቶ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከሁነቶች ስያሜ ቀጥሎ ያለውን ማፈናጠሪያ በመጫን ማግኘት ይችላሉ።

- በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ መዋዕለ ንዋይን ማፍሰስ:: ታዳሽ ሀይል፣በራስ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነፃ የኢንተርኔት ትምህርት በእስያ ልማት ባንክ ኢንስቲትዩት ምንጭ
- ከካርበን ነፃን እውን ስለማድረግ: የአየር ንብረት ለውጥ አዎንታዊ እርምጃዎች እንዴት ከኮቪድ-19 ማገገምን ያፋጥናሉ?፤ ዌቢናር፣ እ.አ.አ. ጁላይ 2020.ምንጭ
- የአፍሪካ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ፎረም-7ኛ ክፍል ጊዜ: ለውጥን ማስቻል፣ እ.አ.አ. ጁላይ 2020.| ምንጭ
- የውቅያኖስ የውሀ አካል እንደመንታ መፍትሄ: ከአየር ንብረት ለውጥና ከኮሮና ወረርሽኝ ተፅኖዎች ለማገገም፤ ዌቢናር ፣ እ.አ.አ. ጁላይ 2020|ምንጭ
- ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ኮሙኒኬሽን ሲምፖዚየም፣ እ.አ.አ. ጁላይ 2020|ምንጭ
- ፈጠራ ለአየር ንብረት ለውጥ: በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ ነፃ ገበያ-አዳዲስ ህግጋት ለለውጥ፣ እ.አ.አ. ጁላይ 2020|ምንጭ
- የብዝሀ ህይወት ጉባኤ፣ እ.አ.አ. ሴፕቴምበር 2020|ምንጭ
- የኢንተርኔት ስልጠና: በመንግስትና በግል ዘርፍ ትብብር፤ በግል ብቃት ላዩ የተመሠረተና የመስኖ ልማት ውጤታማነትን በማሻሻል ላይ የሚያተኩር ፣ እ.አ.አ. ዲሴምበር 2020 | ምንጭ
- የኢንተርኔት ስልጠና: ለዝቅተኛ የካርበን ልቀት የፖሊሲ ማዕቀፍ ሚና: ከማርቀቅ እስከ ትግበራ (በግል ፍጥነት ላይ የተመሠረተ)፣ እ.አ.አ. ዲሴምበር 2020|ምንጭ

### የሀይል አቅርቦትን በኢትዮጵያ ማዳረስ፤ በፈቃደኝነት ላይ ለተመሰረተ ብሄራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድ (NDC) የመተግበሪያ ሀብት ማሰባሰብ

- በውሀ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተዘጋጀ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም 2.0 (NEP 2.0) ይፋ የሆነው በህዳር 2009 ዓ.ም ሲሆን በ2025 ለሁሉም ታዳሽ የብርሀን ሀይል ለማዳረስ የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ስልት ነው:: ይህ ፕሮግራም አጓጊ ኢላማዎች ቢኖሩትም 35% የሚሆነው በገጠር የሚኖረው ህብረተሰብ ግን እስካሁንም ድረስ ያለ ኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት እየኖረ ይገኛል:: መንግስት ይሄንን የኤሌክትሪፊኬሽን ክፍተት በፀሀይ ሀይል ስርዐትና እና አነስተኛ የሀይል ማሰራጫዎች ለመሙላት የግሉ ዘርፍ ሚና ከፍተኛ ለመሆኑ እውቅና ይሰጣል:: በዋነኛነትም አነስተኛ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሀይል ያለው ገመድ አልባ የኤሌክትሪክ ስርጭት በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶታል::

የሀይል ማሰራጫውን ዘርፍ ለማጠናከር የውሀ፣ መስኖና ኢነርጂ ዘርፍ የመነሻ ጥናት በማጥናት ረገድ ከአለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ጋር በቅርበት እየሰራ ይገኛል:: የዳሰሳ ጥናቱ የሀይል ማሰራጫው ዘርፍ እድገት በፋይናንስና ህጋዊ ቁጥጥር ዙሪያ ያሉት ማነቆዎች ላይ ያተኮረ ነበር:: ከዚህ በተጨማሪም ባለድርሻ አካላት፣ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች መልካም እድሎችንም በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን ለኢነርጂው ዘርፍ የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦችንም አስቀምጧል::

ከማመሳከሪያ (የመነሻ ጥናት) በመቀጠል ሚኒ ግሪዱን ለግብርና፣ ለንግድና በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰራ የኢንዱስትሪ አገልግሎት በመጠቀም፤ እንዴት የተለያዩ ምርቶችን ማምረት እንደሚቻል ጥልቀት ያለው ጥናት ተከናውኗል። ይህም ጥናት ሶስት ክፍሎች ያሉት የምርታማነት ጉዳዮችን የለየ ሲሆን እነሱም (1) የግብርና ግብይት ክላስተር (2) የወተት ማሰባሰቢያ ማዕከል እና (3) የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ የግብርና ግብይት ክላስተርና የወተት ማሰባሰቢያ ማዕከል ከፍተኛ አቅም አላቸው ተብለው የሚታሰቡ ናቸው።

የግብርና ግብይት ክላስተር በተመሳሳይ ምርት ላይ ተሰማርተው ከብዛታቸው ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ (economies of scale) ለማግኘት የተሰባሰቡ አርሶ አደሮች ሲሆኑ የሚመራውም በግብርና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ነው:: ይህ ክላስተር በመቶዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች፣ ሰፊ የሆነ በመቶ ሔክታር የሚገመት ለእርሻ የሚሆን መሬት፣ ጥቃቅን የሆኑ አነስተኛ ገቢ ማስገኛ ንግዶች፣ ሱቆች፣ ጤና ጣቢያና ት/ቤቶችን የያዘ ነው:: እንደ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ቲማቲምና ሽንኩርት ያሉ የአትክልትና ፍራፍሬ አይነቶች ለአርሶ አደሩ ከፍተኛ የሆነ ገቢ የሚያስገኙ ቢሆኑም እነዚህ ለመመረት መስኖ ይፈልጋሉ::

# ልዩ ልዩ ህትመቶች

## የኤን.ዲ.ሲ. የኪስ ማስታወሻ




የ.ተ.መ.ድ. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመቀነስ በሀገራት እየተዘጋጀ የሚተገበረውንና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድን አስመልክቶ በየጊዜው ለአተገባበር መርጃ የሚሆኑ የኪስ ማስታወሻዎችን ያዘጋጃል:: መተግበሪያ መመሪያው በዚህ እትሙ የተከለሰውን የፓሪስ ሩል ቡክ ድንጋጌዎች አካቷል::

መመሪያው አዳዲስ ሀሳቦችን ለምሳሌ የሀገራት የኤን.ዲ.ሲ. ዕቅድ ምን ምን ጉዳዮችን ያካትታል? ሀገራት ዕቅዳቸውን ከመተግበር ረገድ ምን ምን መረጃዎችን በግልፅነትና በተጠያቂነት መንፈስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል? ሀገራት ተግባራቸውን አስመልክቶ በአግባቡ አደራጅተው መያዝና ማቅረብ የሚገቡዋቸው ጉዳዮች ምንድናቸው? ዕቅዳቸውን ማሳካት ካልቻሉስ ምን ይሆናሉ? ለሚሉት ምላሽ ይሰጣል:: ምንጭ

## የፓሪስ ስምምነት ጋይድ




የአውሮፓ የአቅም ግንባታ ድጋፍ (ECBI) በቅርቡ የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነትን የተመለከተ የአተገባበር መመሪያ ይፋ አድርጓል:: ይህ መተግበሪያ መመሪያው እ.አ.አ. በ2018 የወጣውን የስምምነቱ መተግበሪያ መመሪያንም ያካተተ ነው:: መመሪያው በተጨማሪነት የታዳጊ ሀገራት የዘርፉ ፖሊሲዎችና ህጎች በአተገባበሩ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን እንድምታም አካቷል::ምንጭ

## መሬትና የውሀ አካላትን የተመለከተው የመንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ፓናል ልዩ ሪፖርት፣ ለአፍሪካ ምን ይጠቅማል?




ሲ.ዲ.ኬ.ኤን. በቅርቡ ለንባብ ባበቃቸው ሁለት ህትመቶች የአይ.ፒ.ሲ.ሲ. ልዩ ሪፖርት በአየር ንብረት ለውጥና በመሬት እንዲሁም የውሀ አካላትንና በበረዶ የተሸፈኑ የምድር ክፍሎችን አስመልክቶ ለውሳኔ ሰጪ አካላት ያወጣውን መረጃ ተንትኗል:: የተቋሙ ህትመቶች በተጨማሪም የአፍሪካ ውቅያኖሶች እና መሬትን የተመለከቱ ጥናቶችን አስነብቧል:: ለተጨማሪ መረጃ እነዚህን ማስፈንጠሪያዎች ይጫኑ:
http://www.cdkn.org/oceanreport
http://www.cdkn.org/landreport

**ከገፅ 4 የቀጠለ...**

የግብርና ግብይት ክላስተር ዋነኛ የ አነስተኛ የሀይል ማሰራጫዎች ተጠቃሚ ሲሆኑ፤ ይህም ለመስኖ፣ ለጥቃቅን ቢዝነሶች፣ ሱቆች፣ ጤና ጣቢያና ት/ቤቶች ነው:: በዚሁ ክላስተር ውስጥ የሚገኙ የግብርናው ዘርፍ ተጠቃሚዎች ትክክለኛውን የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ ወጪ ሲከፍሉ ይህም ሌሎችን ተጠቃሚዎች ለመደጎም ይረዳል:: የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በርካታ መጠን ያለው በቅርብ ጥልቀት ከ30 ሜትር ባነሰ ርቀት የሚገኝ የጉድጓድ ውሀ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል እንደሚገኝ ያረጋገጠ ሲሆን ይህም ለአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለእንስሳትና ለማህበረሰቡ በቀላሉ ለመስኖ ጥቅም መዋል የሚችል ነው::

**የወተት ማሰባሰቢያ ማዕከል፤** ኢትዮጵያ በአለም በእንስሳት ሀብት አምስተኛ ደረጃ ላይ ያለች እና ከዚህም በተጨማሪ ለወተት ምርት ተስማሚ የሆነ ምቹ የአየር ጠባይ ያላት ብትሆንም ከሳሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሃገራት ዝቅተኛ የወተት ምርት ያላት ሀገር ሆና ትገኛለች። በዚህም ሳቢያ በወተት ተዋፅኦ አኳያ ወደ ውጭ ከምትልከው ጋር ሲነፃፀር የምታስገባው ምርት ይበልጣል። የወተት ምርቱ ባብዛኛው እየተካሄደ የሚገኘው በዝናብ ውሀ አቅርቦት ብቻ ላይ ጥገኛ በሆነው የገጠሩ ማህበረሰብ አካባቢ በመሆኑ ይህ በወተት ምርትና የመኖ አቅርቦት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። አብዛኛዎቹ የወተት ማሰባሰቢያ ማዕከሎች የኤሌክትሪክ አቅርቦት ስለሌላቸው ወተትን አቀዝቅዞ ለተወሰነ ጊዜ ሳይበላሽ ማስቀመጥ አይቻልም። ስለዚህ በዚህ ዘርፍ ላይ የሚደረግ በአነስተኛ የሀይል ማሰራጫዎች ግንባታ ላይ የሚደረግ ልማት ምርታማነትን ያሳድጋል፤ በገጠር ለሚገኘው አርሶ አደር የተሻለ መተዳደሪያ ሲፈጥር ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ አልበገሬነትንም ያረጋግጣል።

**ቀጣይ አቅጣጫ፣ ሚኒ ግሪድ ኢንቨስትመንት ጉዳይና ከቅንጅት ጉዳዮች**

በግብርና ግብይት ክላስተር ባተኮረ መልኩ፤ የውሀ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለተመረጡ 10 የአትክልትና ፍራፍሬ ግብርና ግብይት ክላስተር የመዋለ ንዋይ ማፍሰስ ጉዳይ እና የአዋጭነት ጥናት እያዘጋጀ ይገኛል:: እነዚህ መስኮች ለአነስተኛ የሀይል ማሰራጫዎች ሰርቶ ማሳያ ማዘጋጃ የሚሆን ከአደጋ ነፃ የሆነ ፋይናንስ ለማግኘት፤ በኢንቨስትመንት መድረኮች ላይ እና የበጀት ጥሪዎች ላይ ይቀርባሉ። እነዚህ የአነስተኛ የሀይል ማሰራጫዎች አካባቢዎች ላይ በቅርበት የክትትል ስራና መረጃ የሚሰራ ሲሆን ይህም የውሀ ማውጣቱን ስራ ይደግፋል:: ከዚህ በተጨማሪ እየተካሄደ ላለው የNDC ክለሳ ሂደት ግብዓት በሚሆን መልኩ ይሄንና ሌሎች መስመር አልባ የኤሌክትሪክ ፕሮገራሞችን ለማቀናጀትና የአነስተኛ የሀይል ማሰራጫዎች ፈንድ ስትራቴጂ የመቀረፅ ስራ ተጀምሯል።

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዴሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150
ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com
ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

## ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም፡፡

## ስራውን የደገፉ አካላት

IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

Supported by:

based on a decision of the German Bundestag

Funded by

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.